# የጤና እንክብካቤዎ ምን ያክል ወጪ እንደሚያስወጣ የሚያብራራ “የቀና መንፈስ ግምት” የማግኘት መብት አልዎት።

**በሕጉ መሰረት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች የተወሰኑ የጤና እንክብካቤ ሽፋን አይነቶች ለሌሏቸው ወይም የተወሰኑ የጤና እንክብካቤ ሽፋን አይነቶችን ለማይጠቀሙ ታካሚዎች የጤና እንክብካቤ  አይነቶች ወይም አገልግሎቶች ከመቅረባቸው በፊት የጤና እንክብካቤ አይነቶች እና አገልግሎቶቹ የሚያስከፍሏቸውን ክፍያ ግምት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።**

- ለየትኛውም የጤና እንክብካቤ አይነቶች ወይም አገልግሎቶች ጠቅላላ የሚጠበቀውን ወጪ የተመለከተ የቀና መንፈስ ግምት ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም ለእንክብካቤው ወይም አገልግሎቶቹ ቀጠሮ በሚያስይዙበት ወቅት የማግኘት መብት አልዎት።  ይህ እንደ የህክምና ምርመራዎች፣ የሚታዘዙ መድሀኒቶች፣ መሳሪያዎችና የሆስፒታል ክፍያዎች የመሳሰሉ ተያያዥ ወጪዎችን ይይዛል።
- ለጤና እንክብካቤ አይነት ወይም አገልግሎት ቢያንስ ከሶስት የስራ ቀናት በፊት ቀጠሮ የሚያስይዙ ከሆነ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ወይም ተቋምዎ ከቀጠሮው በኋላ በአንድ የስራ ቀን ውስጥ የቀና መንፈስ ግምት በጽሁፍ የሚሰጥዎ መሆኑን ያረጋግጡ።  ለጤና እንክብካቤ አይነት ወይም አገልግሎት ቢያንስ ከ10 የስራ ቀናት በፊት ቀጠሮ የሚያስይዙ ከሆነ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ወይም ተቋምዎ ከቀጠሮው በኋላ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የቀና መንፈስ ግምት በጽሁፍ የሚሰጥዎ መሆኑን ያረጋግጡ። በተጨማሪም የትኛውንም የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ተቋም የእንክብካቤ ወይም አገልግሎት ቀጠሮ ከማስያዝዎ በፊት የቀና መንፈስ ግምት እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።  ይህን ካደረጉ የጤና እንክብካቤ አቅራቢው ወይም ተቋሙ ጥያቄ ባቀረቡ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የቀና መንፈስ ግምት በጽሁፍ የሚሰጥዎ መሆኑን ያረጋግጡ።
- የትኛውም የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ተቋም ከቀና መንፈስ ግምቱ ቢያንስ በ$400 የሚበልጥ ክፍያ ካስከፈልዎ በክፍያው ላይ አለመስማማት ይችላሉ።
- የቀና መንፈስ ግምትዎን እና የክፍያዎን ኮፒ ወይም ምስል መያዝዎን ያረጋግጡ።

የቀና መንፈስ ግምትን በተመለከተ ስላሉዎት መብት ጥያቄዎች ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **cms.gov/nosurprises/consumers** ን ይጎብኙ፣ በ **FederalPPDRQuestions@cms.hhs.gov** ኢሜይል ይላኩ ወይም በስልክ ቁጥር **800.985.3059** ይደውሉ።

የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ብሮሸር ይጠይቁ ወይም **corewellhealth.org/policies** ን ይጎብኙ

Corewell Health © 10.2023